# እሽሩሩ - ሩሩ - ኦሶ ሃዬ ሃዬ

(ከገንባው)

የምጠላህ ልጄን፣ አዝዬህ ቂምን፣
“እሽሩሩ” የምልህ፣ እስከመቼ ይሆን?
ይሁን ታዘል ልጄ፣ ማልቀሱን ተውልኝ፣
ድምፁን በቀን ጠሀይ፣ አፍነው ያሳጡኝ፣
“ደርስኩልሽ” ሲለኝ፣ ደርሰው የደፉብኝ፣
ደፍተው ሲያበቁ፣ ‘ሌባ’ ያሰኙብኝ፣
መቼ ንብረታቸውን፣ ባንካቸውን ደፍሮ፣
ጣቱን ቀስሮ እንጂ፣ መቼ እጁን ሰንዝሮ፣
ገዳዩስ ድምፁ ነው፣ ጠንቀኛው ጉሮሮ።
ልጄ አፍህን ዝጋ! አታልቅስ ላይረባ፣
በየአምስት አመቱስ፣ እኔስ ለምን ላንባ፣
ድምጽህ ጠላትህ ነው፣ ጉልበትህን ገንባ።
ታገስ ታዘል ልጄ፣ ይላጥ የኔ ጀርባ፣
‘እጣችን’ መኖርን፣ ፍርድ እየተዛባ፣
ላሁን እንዳልለው፣ ቆይልኝ ባንቀልባ።
ይሁን ‘እሽሩሩ’፣ ተዳፍነህ ጋም ልጄ፣
የሚቆለመም ጣት፣ እንደሌለው እጄ።
አስክታሳይልኝ እሽሩሩ - ሩሩ
የአበሻ ነውና ‘እሽሩሩ - ሩሩ’
የሚጫርን እሳት እሽሩሩ - ሩሩ፣
አዳፍኖ ማደሩ፣ እሽሩሩ - ሩሩ።
እሽሩሩ ልጄ፣ ኦሶ ሃዬ ሃዬ፣
እኛ ምርጫ የለንም፣ ላኑርህ አባብዬ

(እ.ኤ.አ. 10/30/2009)

---

ኦሶ ሃዬ ሃዬ - ያው የሰሜነኛው ‘እሽሩሩ ማሞ’ መሆኑ ነው - በደቡብ